# የቪክቶሪያዊ አፍሪካዊ ማሕበረሰባት ድርጊት እቅድ

## በቀላል አማርኛ አጭር መግለጫ

ሙሉ የእቅድ መግለጫን ለማንበብ በድረገፅ **www.multicultural.vic.gov.au** ላይ መግባት። **የ10 ዓመት የአፍሪካዊ ማሕበረሰባት ድርጊት እቅድ ዋና ዓላማው እንግዳ ተቀባይ የሆነ ማሕበረሰብ ለመገንባት፤ ውጤትን ማሻሻልና የቪክቶሪያዊያን አፍሪካዊ ቅርስ የሚቀጥልበትን እድል ለመፍጠር ነው።**

በቪክቶሪያ የአፍሪካዊ ማሕበረሰባት የድርጊት እቅድ የወጣው በቪክቶሪያ አፍሪካዊ ማሕበረሰብ በኩል ነው።

የዚህን እድገት የመራው የአፍሪካዊ ሚኒስትሪያል የሥራ ቡድን (AMWG) ትውልደ አፍሪካውያን በሆኑ ከተለያዩ ቡድን በተውጣጡ 22 ሰዎች ከጥቅምት/October 2016 እስከ የካቲት/February 2018 ባለው ጊዜ ነው። በዚህን ጊዜ ውስጥ በቪክቶሪያ የሚኖሩ በመቶዎች የሚቆጠሩ ትውልደ አፍሪካውያኖች ሃሳባቸውንና አመለካከታቸውን ለእቅዱ ግንባታ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

የድርጊት እቅዱ ምላሽ የሚሰጠው በደንብ ለታወቁ ጉዳዮች ሲሆን እንዲሁም ሰዎች ያላቸውን ህይወት/ኑሮ ለማሻሻል የሚያስችል ውሳኔ እንዲያካሂዱ በማበረታታትና በመደገፍ ላይ ያለመ ይሆናል።

## ማሕበረሰባት በአመራር የሥራ ድርሻ ስለመጫወት

በቪክቶሪያ አፍሪካዊ ማሕበረሰባት ውስጥ ላሉ ሰዎች የድርጊት እቅዱ የሚጠይቀው በመፍትሄዎች ላይ ተሳታፊ በመሆን በራሳቸው አመራር እንዲፈጸም ነው። ይህ ትብብርን፤ መገልገያን፤ የሙያ ብቃትን፤ እውቀትንና ዘላቂ ለውጥን እንዴት መፍጠር እንደሚቻል ማወቅን እንደሚያስፈልግ ነው።

የድርጊት እቅዱ ደህንነትን ለማሻሻል ለመርዳት መንግሥትን፤ እንዲሁም የሲቪል፤ የግል፤ የአካዳሚክ፣ የበጎ አድራጎት ክፍሎችን ከአፍሪካዊ ማሕበረሰባት ጋር እንዴት በቅርበት ለመሥራት እንደሚችሉ እንዲያሳስቡበት ይጠይቃል።

የድርጊት እቅዱ በአራት ቁልፍ በሆኑ መሰረታዊ መመሪያዎች ይደገፋል:

- የማሕበረሰብ ተሰጥኦን መጠቀም እና ስለሚከተሉት የማወቅ ችሎታ
- ተጠያቂ ሃላፊነት
- በጋር ሆኖ መሥራት
- ዘላቂ ለውጥ ለመፍጠር ትኩረት ማድረግ

## ዘላቂ ለውጥ ስለመሥራት

የድርጊት እቅዱ በስድስት ትኩረት በተደረገባቸው ነጥቦች ላይ ከ250 ድርጊቶች በላይ ሃሳብ አቅርቧል።

የታቀዱት ድርጊቶች ዓላማ ለሁሉ ሰው እድልን በመፍጠር አካል ለመሆን አስተዋጽኦ ለማድረግ እና ልርመበልጸግ ነው።

እነዚህ ድርጊቶቹ ማሕበረሰባት፤ መንግሥትና ሌሎችም በቪክቶሪያ ላሉ ለአፍሪካዊ ማሕበረሰባት ህዝብ በሚሰጡት የመደገፍ ሥራዎች ላይ የተገነቡ ናቸው።

## በድርጊት እቅድ ስድስት የትኩረት መስኮች

1. **ንግድ ሥራ**

   በኢኮኖሚ ዙሪያ የአፍሪካዊ ቪክቶሪያዊያን የፈጠራ ግኝት፤ የንግድ ድርጅትና ኢንቨስትመንት እያደገ ስለመሆን

2. **ሥራ ስለመቀጠር**

   በሁሉም ዘርፎች የሙያ ችሎታ ማጠናከርና ተገቢ የሆነ ሥራ ለማግኘት መንገድ መክፈት

3. **ትምህርትና ሥልጠና**

   ጠንካራ መሰረታዊ ትምህርትን ማጠናከርና ለሕይወት ኑሮ የሚሆን የሙያ  ችሎታን ማግኘት

4. **ጤና እና ደህንነት**

   የሁሉንም ሰዎች ማሕበራዊ፤ ስሜታዊ እና አካላዊ ደህንነትን ማዳበር

5. **ማሳተፍ እና ብቁ ማድረግ**

   በሰዎች እኩልነት ላይ ስለመርዳት፤ በአግባብና ከአክብሮት ጋር ማስተናገድ

6. **አመራር፤ የቅርብ ትስስር እና ግንኙነት**

   ለጠንካራ ቪክቶሪያ አስተዋጽኦ ስለማድረግ ይህም በጥሩ አመራር፤ የማሕበረሰባት ቅርብ ትስስር እና በሞላው ሕብረተሰብ ዙሪያ ጠንካራ ግንኙነት በማድረግ ይሆናል።

# የድርጊት እቅድ ማጠቃለያ

## ሶስት የተለመዱ ጭብጥ መልእክቶች

ሶስቱ ጭብጥ መልእክቶች ትኩረት ከተደረገባቸው ነጥቦች ጋራ የተለመዱ ናቸው። ድርጊቶችን ለመፈጸም እነዚህ መመሪያ በመስጠት ይረዳሉ።

የተሻለ ተሳትፎ እና ለተሻለ አገልግሎቶች

*በታላቁ የማሕበረሰብ ተሳትፎ አማካኝነት ተስማሚ የሆኑ አገልግሎቶችን ለመገልገልና ለመጠቀም ስለማሻሻል*

አብሮ በመሥራት ችሎታን ስለማዳበር

*አብሮ ጠንክሮ መሥስራትን በመደገፍ ማሕበረሰባት የአመራርና አቀራረብ ችሎታን ማዳበር*

እውቀትንና ማስረጃን ስለማሻሻል

*የማሕበረሰባትን እውቀትንና በቂ ማስረጃዎችን መገልገያን ማጠናከር ለወደፊት ድርጊት መመሪያ ይሆናል*



# የትኩረት መስኮችና አርእስቶች

እያንዳንዱ የትኩረት መስክ ለድርጊቱ ሃሳብ ያቀርባል፤ ይህም በአፍሪካዊ ማሕበረሰባት ዙሪያ ላሉት ሰዎች እየቀነሰ ላለ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ደህንነት በጣም ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ምላሽ ይሰጣል።

ከግማሽ በላይ የሆነው የድርጊት ዓላማ ለወጣቶችና ለቤተሰባቸው ለመርዳትና ለማበረታታት ነው።

ይህ የ 10 ዓመት እቅድ እንደመሆኑ፤ አንዳንድ ድርጊቶች በቅርቡ ይተላለፋሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ለወደፊት ለማቅረብ የበለጠ እቅድ ማውጣት ያስፈልጋቸዋል።

## ወደፊት የሚራመበት መንገድ

የዚህ ውጥን ሃሳብ ኃላፊነት በአንድ የመንግስት አካል ወይም በተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል ላይ ብቻ መጣል የለበትም።

የዚህ እቅድ ድርጊት አፈጻጸም በአብሮ መስራት ላይ የተመረኮዘ ይሆናል፡ ይህም ማለት ለአፈጻጸሙ ከተለያየ ማህበረሰባት የተውጣጡ ሰዎችን ድርጅቶችን ብሎም በሁሉም ደረጃ ያሉትን መንግሥታዊ ክፍሎች እና ዘርፎችን ተሳትፎ ያስፈልጋል።

## ለመተግበር ቅድሚያዎች

የ AMWG እንዳለው ወደፊት ለመራመድ መከተል የሚገባ መመሪያ ሶስት ጠቃሚ ጉዳዮች እንዳሉ ነው።

1. ጠንካራ የመንግሥት አስተዳደር እና አብሮ መሥራት
2. በመላው ቪክቶሪያ ያሉት ማሕበረሰባት መሳተፍ
3. ማመዛዘን፤ መቆጣጠር፤ መገምገም እና በእድገት ላይ ሪፖርት ማድረግ

| ትኩረት የተደረገበት መስክ | በታቀደው ድርጊት ላይ የተካተቱ አርእስቶች | |
|---|---|---|
| የንግድ ሥራ | የንግድ ሥራ<br>አብሮ ንግድ መሥራትና አዲስ ፈጠራ | የንግድ ሥራ መርበብ እና አብሮ መሥራት<br>ንግድና ኢንቨስትመንት |
| ሥራ ስለመቀጠር | ለሥራ ዝግጁ መሆን<br>ቀደም ብሎ ትምህርት ላቋረጡና በቅርቡ ለተመረቁ<br>የሥራ መግቢያና ምልመላ | የውጭ አገር ሙያ እና ችሎታ<br>የነበረን ይዞ መቆየትና እንቅስቃሴን መጨመር |
| ትምህርትና ሥልጠና | የቅድሚያ ልጅነት ትምህርት<br>ወደ ትምህርት መስክ ያገናኛል<br>ከትምህርት ቤት መርሃ ግብር በፊትና በኋላ<br>እድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ህጻናትና ወጣቶች | ለጎልማሳ ትምህርትና ስለመማር<br>ለሥራ ልምድና በፈቃደኝነት መሥራት<br>ከፍተኛ ትምህርትና ለሥራ ማስገቢያ የሙያ ሥልጠና |
| ጤና እና ደህንነት | የአእምሮ ጤና<br>የአካል ጤና እና የማይድን በሽታ<br>የቤተሰብ ሁከት | ችግር ላይ ያለ ታዳጊ ወጣት<br>በእድሜ አንጋፋ ለሆኑና ላረጁ<br>ቤተሰቦችን ማጠናከር |
| ማካተትና ብቁ ማድረግ | ለአዲስ መጤ<br>አካለ ጉዳተኛ ለሆኑ ሰዎች<br>በእድሜ አንጋፋ ለሆኑና ላረጁ<br>ጾታና ወሲባዊ ፍላጎት | በፍትህ አሰራር ውስጥ ላሉ ሰዎች<br>ሴቶችና የጾታ እኩልነት<br>ህጻን መከላከያ |
| መሪነት፤ የቅርብ ትስስርና ግንኙነት | የማሕበረሰብ መሪነት<br>እውቀትን ማካፈልና ማስተባበር<br>በመላው ማሕበረሰብ ዙሪያ በቅርበት መተሳሰር<br>ታዳጊ ወጣቶች | መሰረተ ልማትና መገልገያዎች<br>መገናኛ ሚዲያ<br>የአውስትራሊያን ህግ ስለመረዳትና ከባለሥልጣናት ጋር አብሮ መሥራት |

VICTORIA